**በ 04/1/25 ተሻሽሏል**

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የግሮሰሪ (Groceries) ፕሮግራም
## ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## <u>የፕሮግራሙ መሰረታዊ ነገሮች</u>

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የግሮሰሪ (Groceries) ፕሮግራም ምንድን ነው?**

የሞንትጎመሪ ግሮሰሪ ፕሮግራም ከ ኢንስታካርት ፍሬሽ ፈንድስ (Instacart Fresh Funds)[1] ጋር በመተባበር እቤት ድረስ ሊቀርቡ ወይም በአካባቢው ካሉ ሱቆች ሊወሰዱ የሚችሉ ትኩስ እና በመደርደሪያ ላይ የተቀመጡ የምግብ ዕቃዎች በኦላይን መግዛት የሚያስችል አገልግሎትን ይሰጣል፣ እነዚህም ተለይተው የታወቁ እቃዎች በኦላይን መግዛት የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ ነው። ለፕሮግራሙ ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ከ 0 እስከ 18 ዓመት እድሜ ላለ ለእያንዳንዱ ልጅ በየወሩ 100 ዶላር ድጋፍ ሊያገኙ የሚችሉ ሲሆን በጠቅላላ እስከ 400 ዶላር ሊቀበሉ ይችላሉ።

ይህ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የምግብ ስርአት ሪዚሊያንስ (Montgomery County Office of Food Systems Resilience(OFSR)) እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰባዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) በጋራ በመተባበር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ የሚኖሩ ህጻናት አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የሚያግዝ አዲስ ፕሮግራም ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ምክር ቤት የሕጻናት ረሃብን ለማስወገድ የስትራቴጂክ እቅድ የውሳኔ ሃሳቦችን ተግባራዊ ለማድረግ እና በበጀት ዓመት 25 (FY25) በካውንቲው የስራ ማስኬጃ በጀት ውስጥ ለፕሮግራሙ ቀጣይነት የሚሆን ተጨማሪ ገንዘብ ለመደገፍ በልዩ የበጀት ድጎማ #24-37 በዲሴምበር 2023 ለዚህ ፕሮግራም 1.8 ሚሊዮን ዶላር አጽድቋል።

**በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ማን መሳተፍ ይችላል?**

ለዚህ ፕሮግራም ብቁ ለመሆን የቤተሰቡ አባላት የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-

- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ
- በተጨማሪ የተመጣጠነ ምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP) ውስጥ **ተሳታፊ ያልሆነ (ች)** ከ 18 አመት በታች የሆነ(ች) ልጅ ያላቸው፣ እና
- ገቢዎ ከፌዴራል የድህነት ደረጃ ከ 400% በታች ሊሆን ይገባል (ለምሳሌ፣124,000 ዶላር /በዓመት 4 የቤተሰብ አባላት ላሉት ቤተሰብ)
    - የገቢዎ መጠን ለፕሮግራሙ ብቁ እንደምያደርግዎት ለማረጋገጥ እንዲችሉ፣ ይህንን ፌዴራል የድህነት ወለል (FPL) ካልኩሌተር መጠቀም ይችላሉ፣ https://home.mycoverageplan.com/fpl.html[https://home.mycoverageplan.com/fpl.html](https://home.mycoverageplan.com/fpl.html)።

**ቤተሰቦች ማመልከቻውን ማጠናቀቅ እንዲችሉ የሚከተሉትን ሰነዶች ማስገባት አለባቸው፡-**

- የገቢ ማረጋገጫ እንደ ፔይስታብ (pay stubs) ወይም ከአሰሪ የተጻፈ ደብዳቤ።

---

[1] *ፍሬሽ ፈንድስ (Fresh Funds) የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ትኩስ እና ፍሮዝን የሆኑ ምግቦችን ለመግዛት እንዲችሉ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ የኢንስታካርት (Instacart) ፕሮግራም ነው።*

- የሚሰራ የፎቶ መታወቂያ ማለትም እንደ የመንጃ ፈቃድ፣ የሜሪላንድ መታወቂያ ወይም የወላጅ(ዎች) ወይም የአሳዳጊዎች ፓስፖርት።
- የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫ ማለትም አሁን የሚኖሩበትን አድራሻ የሚያሳይ የከራይ ውል፣ከአከራይ የተጻፈ ደብዳቤ፣ የመንጃ ፍቃድ ወይም የፍጆታ መገልገያ ቢል።
- በፕሮግራሙ ውስጥ ለሚሳተፉ ሁሉም ልጆች በመንግስት የተሰጠ ማንነት የሚያረጋግጥ ዶክመንት

**ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣**

- የመጠባበቂያ ኤሌክትሮኒክ የክፍያ አማራጭ ማዘጋጀት (ማለትም፣ ዴቢት ካርድን፣ ክሬዲት ካርድን፣ ጎግል ፔይን፣ አፕል ፔይን፣ ፔይ ፓልን ወይም ክላርና (Klarna)
- ድጋፉን ለማግኘት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን መተግበሪያ (ፕላትፎርም) መጠቀም መቻል

**ይህ ፕሮግራም ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?**

ይህ ፕሮግራም ጥቅማጥቅሞችን **ለአንድ አመት** ለመስጠት እንዲችል የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ሲሆን ይህም ሊራዘም ይችላል። የፕሮግራሙ ጥቅማጥቅሞች እስከ ጁላይ 15፣ 2026 ይቀጥላሉ።

**በፕሮግራሙ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆን ቤተሰብ ምን ያህል የገንዘብ ድጋፍ ያገኛል?**

የፕሮግራሙ ተሳታፊ ቤተሰቦች ከ 18 አመት በታች ለሆነ ለእያንዳንዱ ለፕሮግራሙ ብቁ ለሆነ ልጅ በወር 100 ዶላር ፣በአጠቃላይ እስከ 400 ዶላር ድረስ ያገኛሉ።

## የኢንስታካርት ፍሬሽ ፈንድስ (Instacart Fresh Funds) ድጋፎችን በተመለከተ፡-


**በዚህ ፕሮግራም የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል?**

ቤተሰቦች በፕሮግራሙ ውስጥ ከተመዘገቡ በኋላ የኢንስታካርት ፍሬሽ ፈንድስ (Instacart Fresh Funds) አካውንት እንዴት መክፈት እንደሚችሉ መመሪያዎች ይደርሳቸዋል። ተሳታፊ ቤተሰቦች በኢንስታካርት (Instacart) አካውንታቸው በኩል የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን የኢንስታካርት (Instacart) ድህረ-ገጽን ወይም አፕሊኬሽንን ተጠቀመው ግዢዎችን ማከናወን ይችላሉ ። የቤተሰቡ አስተዳዳሪ በፕሮግራሙ አማካኝነት ለቤተሰባቸው ያለውን አጠቃላይ ወርሃዊ ድጋፎች ለማግኘት በኢንስታካርት ፍሬሽ ፈንድስ (Instacart Fresh Funds) አካውንታቸው (account) በኩል ልዩ ኮድ ይቀበላሉ። ገንዘብ ድጋፉ በየወሩ በ 15 ኛው ቀን ወይም በሚቀጥለው የስራ ቀን (በአጠቃላይ ለአንድ ለፕሮግራሙ ብቁ ልጅ በወር 100 ዶላር ፣ እስከ 400 ዶላር ድረስ) በአካውንቱ ውስጥ ቀጥታ እንዲገባ ይደረጋል።

የኢንስታካርት ፍሬሽ ፈንድስ (Instacart Fresh Funds) አካውንት እንዲሰራ (activate) ተሳታፊዎች ሌላ አማራጭ የክፍያ መንገድ ማቅረብ አለባቸው። የኢንስታካርት ፍሬሽ ፈንድስ (Instacart Fresh Funds) ዴቢት ካርድን፣ ክሬዲት ካርድን፣ ጎግል ፔይን፣ አፕል ፔይን፣ ፔይ ፓልን፣ ወይም ክላርና (Klarna) ለመቀበል እንዲችል ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

**በዚህ ፕሮግራም ምን ዓይነት ዕቃዎች ሊገዙ ይችላሉ?**

ቤተሰቦች የኢንስታካርት (Instacart) ፕሮግራምን ከሚቀበሉ የመሸጫ ሱቆች የተመረጡ ምግቦችን እና መጠጦችን መግዛት ይችላሉ። ለፍሬሽ ፈንድስ (Fresh Funds) ፕሮግራም ብቁ የሆኑት "Fresh Funds" የሚል ምልክት አለባቸው።




**በአማራጭነት ከሰጠሁት ክፍያ መፈጸሚያ መቼ ነው ክፍያ የሚወሰደው?**

በአማራጭነት ከተቀመጠው ክፍያ መፈጸሚያ በተለያዩ ምክንያቶች ክፍያ ሊወሰድ ይችላል። ለማጠቃለል፣ በአማራጭነት የተቀመጡት የክፍያ መፈጸሚያዎች በሚከተሉት ምክኒያቶች ክፍያ ሊፈጸምባቸው ይችላል:-

- ለፕሮግራሙ ብቁ ያልሆኑ እቃዎች:- ደንበኞች በሚገዙበት ጊዜ የፍሬሽ ፈንድስ አይኮንን (Fresh Funds icon) በመመልከት እቃው በፍሬሽ ፈንድ ፕሮግራም ውስጥ የተካተተ መሆኑን ማየት ይችላሉ። ለፕሮግራሙ ብቁ ያልሆኑ እቃዎች በደንበኛው በኩል በአማራጭነት በተቀመጡት የክፍያ መፈጸሚያዎች በኩል እንዲከፍሉ ይደረጋሉ።
- በቂ ያልሆኑ የገንዘብ መጠኖች:- ከጠቅላላው የፍሬሽ ፈንድስ (Fresh Funds) ቀሪ ሂሳብ በላይ የሚበልጡ ክፍያዎች በደንበኛው በኩል በአማራጭነት በተቀመጡት የክፍያ መፈጸሚያዎች በኩል እንዲከፍሉ ይደረጋሉ።
- ክፍያ በሚፈጸምበት ጊዜ ፍሬሽ ፈንድስን (Fresh Funds) የሚለውን ካልተመረጡ ክፍያው በደንበኛው አማራጭ የክፍያ መፈጸሚያ በኩል ይከናወናል።
- ክፍያ ከተፈጸመ በኃላ ቲፕ ስለመስጠት:- ክፍያ ከተፈጸመ በኃላ የሚሰጥ ቲፕ በፍሬሽ ፍንድስ (Fresh Funds) በኩል ሊከፈል ይችላል። ክፍያ ከተፈጸመ በኃላ የሚሰጥ ቲፕ በደንበኛው አማራጭ የክፍያ መፈጸሚያ በኩል እንዲከፍል ይደረጋል። ከክፍያ በኋላ የሚፈጸም ክፍያ ማለት ደንበኛው በኢንስታግራም ፕላትፎርም (Instacart platform) የግዢ ትእዛዝ ካስተላለፉ በኃላ የሚደረግ ክፍያ ነው።. የኢንስታካርት (Instacart) ፕላትፎርም እቤት ድረስ ለሚመጡ ትእዛዞች የ10% ቲፕ (tip) እንዲሰጥ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፣ ነገር ግን ደንበኞች በግዢ ጊዜ ያለውን የቲፕ መጠን መለወጥ ወይም የሚሰጠውን ቲፕ ማውጣት ይችላሉ።
- እቃዎችን መተካት
- ተመዝነው የሚገዙ እቃዎች
- የፍቃድ መያዣ Authorization holds

**ቤተሰቦች የፍሬሽ ፍንድ (Fresh Funds) ገንዘባቸውን ተጠቅመው በኢንስታካርት (Instacart) በኩል ያዘዙት ምግብ እንዴት ይደርሳቸዋል?**

ቤተሰቦች እንደሚገዙበት ሱቅ አሰራር መሰረት እቤት ድረስ እንዲመጣላቸው ወይም ከመሸጫ ሱቁ እራሳቸው ለመውሰድ (pick up) የሚያስችላቸውን አማራጮችን መምረጥ ይችላሉ።

- ተሳታፊው እቃውን የሚረከብበትን መንገድ ከመረጠ በኋላ፣ ኢንስታካርት (Instacart) የታዘዘውን ግዢ (order) ግዢውን ወደ ሚያከናውነው ግለሰብ (shopper) ያስተላልፋል። ግዢውን የሚፈጸመው ግለሰብ ወደ ግሮሰሪ በመሄድ የፕሮግራም ተሳታፊውን ትዕዛዝ ይገዛል፣ ከዚያም አካውንቱ ላይ ወደ ተተቀሰው አድራሻ በተቀመጠው የማስረከቢያ ጊዜ ውስጥ ያደርሳል።
- የፕሮግራሙ ተሳታፊ የመሸጫ ሱቁ ድረስ በመሄድ ለመውሰድ (pick-up) ከመረጠ፣ ግዢውን ሚያከናውነው ግለሰብ ተሳታፊው ቤተሰብ ከመሸጫው ቦታ ለመውሰድ ( pick-up) እንዲችል እቃዎችን በትዕዛዙ መሰረት ያዘጋጃል እና ተሳታፊው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እቃውን ከሱቁ መውሰድ ይኖርበታል።

በመሸጫ ሱቁ እና በእቃዎቹ አቅርቦት ላይ በመመስረት ትዕዛዞቹ በተመሳሳይ ቀን ሊታዘዙ እና ሊቀርቡ ይችላሉ ወይም በቀጣይ ባሉ የተለያዩ ቀናት እንዲመጡ አስቀድመው ሊታዘዙ ይችላሉ ።

እባክዎን የፍሬሽ ፍንድስ (Fresh Funds) የገንዘብ ድጋፍ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ቤተሰብ ብቻ እንዲጠቀምባቸው የታሰቡ መሆናቸውን ልብ ይበሉ። እቤት ድረስ ማስረከብ የሚቻለው ቤተሰቡ ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት በሚመዘገብበት ወቅት ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰባዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) በሰጠው አድራሻ መሰረት ብቻ ነው።

**በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የትኞቹ የምግብ መሸጫ ሱቆች ይሳተፋሉ?**

ተሳታፊዎች በኢንስታካርት (Instacart) ድህረ-ገጽ ላይ ከተዘረዘሩት ከማንኛውም ሱቆች ይህንን ፕሮግራም በመጠቀም በፍሬሽ ፈንድ በኩል የሚፈቀዱ እቃዎችን መግዛት ይችላሉ። ተሳታፊው ቤተሰብ አካውንት ሲከፍት የመረጠውን የመላኪያ አድራሻ ያስገባል እና በአድራሻው መሰረት በፕሮገራሙ ውስጥ የሚሳተፉ የምግብ መሸጫ ሱቆች ዝርዝር ተለይቶ ይቀመጣል።